# የመጽሐፈ እስክንድር የትውልድ ሐረግ ምንነትና አንድምታ

ጥበቡ አንተነህ[1]

የዚኽ ጥናት መነሻ ሐሳብ የታላቁ እስክንድር (Alexander the Great) ታሪክ በተለያዩ የብራና ቅጅዎች (Manuscript copies) ተመዝግቦ መገኘቱና በዚኽም ምክንያት የይዘት ልዩነት መኖሩ፣ ከብራና ቅጅዎች ብዛት የተነሳም የትኛው የብራና ቅጅ ከየትኛው የብራና ቅጅ እንደተቀዳ መለየት አለመቻሉ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡ ፡ ዋና ዓላማውም የመጽሐፈ እስክንድርን የብራና ቅጅዎች (Manuscript copies) በመሰብሰብ በ 'ስቴማቲክ ስልት' (Stemmatic method) የጥናት ዘዴ የመጽሐፉን የትውልድ ሐረግ (Stemma Codicum)[2] ማሳየት ነው፡፡ በጥናቱም አራት የመጽሐፈ እስክንድር የብራና ቅጅዎች (copies) የተካተቱ ሲኾን ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ አራቱም ቅጅዎች ከአንድ የዘር ሐረግ ለመቀዳታቸው የወል የገጸ ንባብ ስህተቶቻቸው (Archetype errors) ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሦስቱ ቅጅዎች (ሀ፣ ለ እና ሐ) ከቅጅ "መ" በተለየ መንገድ ከአንድ የዘር ሐረግ ለመቀዳታቸው አመልካች ዐቢይ የገጸ ንባብ ስህቶቶቻቸው (Conjunctive errors) ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል ቅጅ "ሀ" እና "ለ" ደግሞ ከ "ሐ" በተለየ መልኩ ከሌላ የዘር ሐረግ እንደተገኙ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ስለኾነም የመጀመሪያው መጽሐፈ እስክንድር (Vorlage) ልጅ (መ)፣ የልጅ ልጅ (ሐ)፣ የልጅ ልጅ ልጆች (ሀ እና ለ) እንዳሉት ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ስለዚኽ ቅጅዎች ባሏቸው የእጅ ጽሑፎች ላይ ትንተና ከማድረግ በፊት ቅጅዎቹን ማነጻጸር (Collate) የቴክስቱን የተሟላ መልእክት ለመረዳት ወሳኝ ሚና እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

**ቁልፍ ቃላት፤** የብራና ቅጅዎች፣ የትውልድ ሐረግ፣ የወል የገጸ ንባብ ስህተት (Archetype error)፣ ዐቢይ ስህተት (Conjunctive error)።

## የጥናቱ ዳራ

ታላቁ እስክንድር (356- 323 ቅልክ[3]) የነበረ ሲኾን በተለያዩ ግዛቶች ትታወቅ የነበረችውን ግሪክን ወደ አንድ በማምጣት ታላቋ ግሪክን የመሠረተ ስመ ጥሩ ንጉሥ ነበር። በ336 ዓ.ዓ አባቱን ፊሊጶስ 2ኛን ተክቶ ዙፋኑን ከተረከበ በኋላ ከግሪክ አልፎ በመላው ምዕራብ እስያና ግብፅ ወታደራዊ ዘመቻ አድርጓል። በዘመኑም ከግሪክ እስከ ሰሜን ምዕራብ ሕንድ ድረስ በታሪክ ውስጥ ትልቁን ግዛት ፈጥሮ ነበር (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ 1965፡ 241)፡፡ በመኾኑም የዚኽ ስመ ገናና ንጉሥ ታሪክ "በእንተ ሑረቱ ለእስክንድር ንጉሥ" እና "በእንተ ክብሩ ወመንግሥቱ ለእስክንድር ንጉሥ"[4] በሚሉ ኹለት አርእስቶች በግእዝ ቋንቋ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

[1] **የግእዝ ት/ክፍል መምህር፣ ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ**;

email: tibebu.anteneh@bdu.edu.et

[2] **የቤተሰብ ዛፍ** (Family tree or geneological tree) **የሚል አቻ ስያሜ አለው፡፡ በዚህ ጥናት ግን የዘር ሐረግ በሚል ስያሜ ተተክቷል፡፡ ይህም የእጅ ጽሑፎችን የቅጅ ቅጅ ሂደት** (Manuscript transmission process) **ያመላክታል፡፡**

[3] **ቅድመ ልደተ ክርስቶስ**

[4]**ይኽን መጽሐፍ ኢትዮጵያውያን ጸሐፍት በ14ኛው ክፍለ ዘመን የአረበኛውን ቅጅ መሠረት በማድረግ እንዳዘጋጁት ይገመታል፡፡ ከላይ እንደተገለጠው መጽሐፉ "…በእንተ ግብሩ ወመንግሥቱ ለእስክንድር ንጉሥ ፍቁረ እግዚአብሔር…."በሚል ርእስ ይጀምራል፡፡ ምንም እንኳን እስክንድር ጣኦት አምላኪ እንደነበር በተለያዩ ምንጮች የሚገኝ ቢኾንም ይህን መጽሐፍ ግን እስክንድርን ክርስቲያናዊ ገጸ**

ነገር ግን የዚኽ ጥናት ዋና ትኩረት የኾነው መጽሐፈ እስክንድር ወይም በእንተ ሑረቱ ለእስክንድር ንጉሥ (‘የእስክንድር ጉዞ’) በሚል ርእስ የንጉሡን ታሪክ ግነት በተሞላበት መልኩ በስፋት ያትታል (ሉዚኒ፣ 2003: 195፣ ከበደ ሚካኤል፣ 1947፡ 1)፡፡ የዚኽ ቅጅ የመጀመሪያው ጽሑፍ (Urtext) እስክንድር ከሞተ ከ500 ዓመታት በኋላ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ድልክ[5] በእስክንድርያ በግሪክኛ እንደተጻፈ ይገመታል (ሲድራስ፣ 2016: 39፣ ወሎሆጅያን፣ 1969:1)፡፡ የጸሐፊው ስምና ማንነት ግን አይታወቅም (ሉዚኒ፣ 2003: 195)፡፡ መጽሐፉ ወደ እብራይስጥ፣ ላቲን፣ ሱርስጥ፣ ቅብጥ፣ አረብኛ፣ ግእዝ እና ወደ ሌሎችም የምዕራባውያን ቋንቋዎችም በተለያዩ ዘመናት ተተርጉሟል፡፡ የዚኽ የግእዝ ቅጅ ግን በ16ኛው ክ/ዘመን ከአረብኛ ወደ ግእዝ በእጨጌ እንባቆም እንደተተረጎመ ይገመታል (ሉዚኒ፣ 2003: 195)፡፡ ኾኖም ይኽ የመጀመሪያው የግእዝ ትርጉም (Ge’ez original version) የጠፋ ቢኾንም አሁን በአራት የተለያዩ ቅጅዎች ይገኛል (ጥበቡ፣ 2020)፡፡ እነዚኽ ቅጅዎች የተለያየ ገጸ ንባብ (Variant reading) ያሳያሉ፡፡ ይኽ የኾነበትም ምክንያት በቅጂ ሂደት (Copying process) እያንዳንዱ ገልባጭ (Scribe) ከቅርጸ ፊደል (Graphic variant)፣ ከቃላት መረጣ፣ ከዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የትረካ ስልት ጀምሮ እስከ ቴክስቱ መልእክት ድረስ በቴክስቱ ላይ በሚያደርገው ግላዊ እርማት (Correction) በቴክስቱ ላይ ለውጥ (Innovation) በመፍጠሩ ነው፡፡ በመኾኑም እያንዳንዱ ቅጅ የጸሐፊውን ወይም የደራሲውን መልእክት (The author’s original message) በተሟላ መልኩ ሊያስተላልፍ ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ ከቅጅዎችም መካከል የትኛው ቅጅ የተሻለ ገጸ ንባብ እንዳለው ለማወቅ ኹሉንም ቅጅዎች ሰብስቦ ገጸ ንባባቸውን በማወዳደርና በማነጻጸር (through collation) በተመሳከረ አርትዖት[6] (Critical edition) የጠፋውን የመጀመሪያውን ቴክስት (The lost original text) መተካት ባይቻልም ለጠፋው ቅርብ የኾነ ቴክስት (A text supposed to be closest to the lost original) ማሳየት ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል (ማስ፣ 1958: 1፣ ሮቢንስ፣ 2007፡ 89 እና ዊትዝል፣ 2014፡ 3)፡፡ ስለዚኽ የመጽሐፈ እስክንድር ቅጅዎችን ገጸ ንባባቸውን በማመሳከር የትኛው ቅጅ ከየትኛው እንደተቀዳ፣ የትኛው ቅጅ ለጠፋው የመጀመሪያው ድርሰት ቅርብ ወይም ሩቅ እንደኾነ ማሳየት[7] የዚኽ ጥናት ዋና ትኩረት ነው፡፡

**የጥናቱ ዓላማ**

የዚኽ ጥናት ዋና ዓላማ ኹሉንም የመጽሐፈ እስክንድርን የብራና ቅጅዎች በመሰብሰብ የመጽሐፉን የትውልድ ሐረግ (Stemma Codicum)[8] ማሳየት ነው፡፡

---

ባሕርይ በማላበስ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ሃይማኖቱ የጸና፣ አማኝ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡

[5]ድኅረ ልደተ ክርስቶስ

[6]Critical edition ለሚለው የእንግሊዝኛ ጽንሰ ሐሳብ ወጥ የኾነ የአማርኛ ፍቺ ስላላገኘሁለት የተመሳከረ አርትዖት የሚለውን አቻ ትርጉም ተጠቅሜያለሁ፡፡

[7]የዚኽ ሐሳብ ዋናው ዓላማ አንዱ ቅጅ የያዘው ገጸ ንባብ ከሌሎች ቅጅዎች ጋር የማመሳከር ሂደት (Data triangulation process) ነው፡፡

[8]የቤተሰብ ዛፍ (Family Tree) በመባልም ይታወቃል፡፡

## የጥናቱ ዘዴ

ይኸ ጥናት በገላጭ የምርምር ንድፍ የተከወነ ሲኾን በዋናነት “ስቴማቲክ ስልትን” (Stemmatic Method) የተከተለ ነው፡፡ ስቴማቲክ ስልት በላኽማን (1793-1851) እና ኒዎ-ላኽማና(ው)ያን ጽንሰ ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ሲኾን፣ ትኩረቱም የእጅ ጽሑፍ ቅጅዎችን ሰብስቦ የጋራ ገጸ ንባብ ስህተትን (shared errors) በመለየት በቅጅዎች መካከል ያለውን ዝምድና (relationship) ማሳየት ነው፡፡ በዚኽም መሠረት ከገዳማት፣ አድባራት፣ አብያተ መጻሕፍትና ከግለሰብ ክምችት (Private collection) አራት የመጽሐፈ እስክንድር ቅጅዎች (Copies) ማለትም EMML 7438[9]፣ BL. 826[10]፣ IES[11] 197 እና Ms QM[12] የተሰበሰቡ ሲኾን ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ ተብለው በቅደም ተከተል ተሰይመዋል፡፡

### የእጅ ጽሑፎች መግለጫ (Description of Manuscripts)

1. ቅጅ ሀ፣ EMML 7438፣ የቅጠል ብዛት 151፣ ባለ ሦስት ዐምድ፣ 32.3 በ28 ሴ.ሜ መጠን ያለው፣ የብራና፣ ገበታው የእንጨት ኾኖ በቆዳ የተሸፈነ፣ በ20ኛው ክ/ዘመን የተከተበ፣

2. ብራና ቅጅ ለ፣ ብሪቲሽ ቤተ መጻሕፍት፣ ለንደን፣ Or. 816፣ የቅጠል ብዛት 155፣ ባለ ኹለት ዐምድ፣ 11⅝ በ7½ ሚ. ሜ መጠን ያለው፣ በ19ኛው ክ/ዘመን የተከተበ፣

---

[9]A Catalogue of Ethiopian Manuscripts Microfilmed for the Ethiopian Manuscripts Microfilm Library, Addis Ababa and For Hill Monastic Microfilm Library, Collegeville, USA (10 vols.), W.F. Macomber.

[10]*The Catalogue of Ethiopian Manuscripts in the British Museum acquired since the Year 1847,* London: British Museum. *See,* Wright, W 1877: 294 (no. 389).

[11]**አድማሱ ጀምበሬ**፣ 1960. **የዲማ ቅ/ጊዮርጊስ የመጻሕፍት ዝርዝር ጥራዝ** 2፣ **ገጽ** 5 **ተመልከት**፡፡ See also, In the United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization (UNESCO 10/63), Ministry of Education and Fine Arts, Department of Fine Arts and Culture (Addis Ababa), 1970. It is also microfilmed by EMIP 613 (Ethiopic Manuscript Imaging Project) led by Prof. Steve Delamarter, George Fox University, Portland, Oregon since 2005 -2010.

[12] **ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም፣ ሁለት እጁ እነሴ፣ ምሥረቅ ጎጃም የሚገኝ የእጅ ጽሑፍ ሲኾን በ** Daniel Ayana, 1989 **የብራና መዝርዝር ውስጥ ይገኛል፡፡** see, A catalogue of Land tenure related Microfilm from Goġġam churches and monasteries recorded between January and July 1989: 6, No. 8 (Daniel Ayana in 1989: 8).

3. ብራና ቅጅ ሐ፣ IES 197፣ የቅጠል ብዛት 105፣ ባለ ኹለት ዐምድ፣ 13 በ22ሴ.ሜ መጠን ያለው፣ በ19ኛው ክ/ዘመን የተከተበ፣

4. ብራና ቅጅ መ፣ ከቀራንዮ መድኃኔዓለም፣ ኹለት እጁ እነሴ ክምችት የተገኘ፣ የቅጠል ብዛት 120፣ ባለ ኹለት ዐምድ፣ 25 በ26 ሴ.ሜ መጠን ያለው፣ በ18ኛው ክ/ዘመን የተከተበ፡፡

**የመጻሕፍተ እስክንድር የትውልድ ሐረግ**

ዘመድ ወይም ዝምድና ወላጅ አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እኅት፣ አኅት፣ አክስት፣ ወገን፣ ዐይነቱና ስሙ ትውልዱና ዘሩ አንድ የኾነ፣ የቅርብ ወይም የሩቅ ዘመድ ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ፣ 1948፡ 422)፡፡ በታሪክ ሂደት ትውልድ ትውልድን በመተካት የሰው ልጅ ዘሩን እንደሚያስቀጥል ኹሉ ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅጅ ቅጅ ሲተላለፉ ቆይተዋል፤ በመተላለፍም ላይ ይገኛሉ፡፡ በመኾኑም ይኽ ጥናት ‘የትውልድ ሐረግ’ የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ በመውሰድ በእጅ ጽሑፍ ቅጅዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ቅርበትና ርቀት ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመኾኑም የሰው ልጅ የዘር ሐረጉ በረዘመ ቁጥር ዝምድናው እንደሚርቅ ኹሉ በእጅ የተጻፉ የብራና መዛግብትም እንዲኹ ከመጀመሪያው ከተቀዱበት ምንጭ (Vorlage) እየራቁና የቅጅ ቅጅ እየኾኑ በሄዱ ቁጥር የይዘትና የሰዋሰዉ ልዩነት በስፋት ያሳያሉ፡፡ ስለኾነም የመጽሐፈ እስክንድር ቅጅዎችን የትውልድ ሐረግ ምንነት ማሳያዎችን ብቻ በማቅረብ የቅጅዎችን የወልና ዐቢይ የገጸ ንባብ ስህተቶችን ከዚኽ በታች እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

የቅጅ “ሀ” ፣ “ለ” ፣ “ሐ” እና “መ” የወል የገጸ ንባብ ስህተቶች (Archetype error)

ቅጅዎች ያሏቸውን የብራና መጻሕፍት የትውልድ ሐረግ በማሳየት ሂደት ለዚኽ ዐላማ የተመረጠውን የብራና መጽሐፍ (ቅጅ) የኹሉም ቅጅዎች (All copies) የወል ስህተት (Archetype error)[13] እና ኹለትና ከዚያ በላይ የኾኑ ቅጅዎች የተጋሩትን ዐቢይ የጋራ ገጸ ንባብ ስህተትን (Conjunctive error)[14] መለየት ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት አራቱም ቅጅዎች ከአንድ ምንጭ መቀዳታቸውን ለአብነት በቀረቡት የወል የገጸ ንባብ ስህተቶች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

1. ወኢርኢኩ፡ አምሳሊሃ፡ ወኢሰማዕኩ፡ <u>ከመ</u>፡ በኀበ፡ ነገሥት፡ ዘከማሃ።

---

[13] *ይኽ የወል ስህተት* (shared error) *ስህተቱ በገልባጩ* (Scribe) *የተፈጠረ ሳይኾን ለቅጅ አብነት ከኾነው ከመጀመሪያው ድርሰት* (Model manuscript) *የተወረሰ* (inherited) *ነው፡፡ ይኽም ስህተት ኹሉም ቅጅዎች ከአንድ ምንጭ መቀዳታቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ነገር ግን በሁሉም ቅጅዎች መካከል የጋራ ስህተት ካልተገኘ ቅጅዎች ከአንድ ምንጭ ያልተቀዱና ከተለያየ ቤተሰብ ወይም የዘር ሐረግ የመጡ መኾናቸውን ያሳያል፡፡*

[14] *ይህ ስህተት ኹለትና ከዚያ በላይ የኾኑ ቅጅዎች የሚጋሩት የስህተት ዐይነት ከመኾኑም ባሻገር በቤተሰብ ዛፍ ምሥረታ* (Family tree or Stemma Codicum) *ሂደት በቅጅዎች መካከል ንኡስ የዘር ሐረግን* (Subfamily) *ለማውጣት ወሳኝ ነው* (ማስ፣ 1958፡ 4)፡፡

*(‘እሷን የሚመስላት አላየኹም፤ በነገሥታት ዘንድም እንደ እሷ ያለ አልሰማኹም፡’)*

ምንም እንኳን ዐረፍተ ነገሩ ከመዋቅር አኳያ ትክክል ቢኾንም በዚኽ አውድ ግን “ከመ” የሚለው ቃል ትርጉም አይሰጥም፡፡ ትክክለኛ ቃሉ “ከመ” ሳይኾን “ክመ” (‘ፈጽሞ’) ማለት ነው፡፡ በዚኽ መሠረት ዐረፍተ ነገሩ፣ ‘እሷን የሚመስላት አላየኹም፤ በነገሥታት ዘንድም ፍጽሞ እንደ እሷ ያለ [ውብ] አልሰማኹም’ ተብሎ ሊስተካከል ይችላል፡፡

2. ወተመየጥነ፡ እምይእቲ፡ ደብር። **ወነሣእነ**፡ ውስተ፡ ገዳም፡ ወበዓታት። ወሐርነ፡ ውስቴቶሙ፡ ፲ወ፭፡ ለያልየ።

*(‘ከዚያችም ደብር ተመለስን፤ ወደ ገዳምና ዋሻዎች ያዝን፤ በውስጣቸውም ዐሥራ አምስት ሌሊቶችን ተጓዝን’)፡፡*

በዚኽ ዐረፍተ ነገር ውስጥ “**ወነሣእነ**” የሚለው ማሰሪያ አንቀጽ ከምንባቡ ዐውድ ጋር የማይሄድ ከመኾኑም በላይ ዐረፍተ ነገሩን ትርጉም አልባ አድርጎታል፡፡ የዐረፍተ ነገር ዐውድ መሠረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ሲስተካከል ይችላል፡፡

ወተመየጥነ፡ እምይእቲ፡ ደብር። **ወተንሣእነ**፡ ውስተ፡ ገዳም፡ ወበዓታት። ወሐርነ፡ ውስቴ ቶሙ፡ ፲ወ፭፡ ለያልየ።

*(“ከዚያች ደብር ተመለስን፤ ከገዳምና ከዋሻዎች ተነሣን፤ በውስጣቸውም ዐሥራ አምስት ሌሊቶችን ተጓዝን”)፡፡*

ከላይ ለአብነት የቀረቡት ሁለቱ የወል ስህተቶች (Archetype errors) አራቱም ቅጅዎች ከአንድ ምንጭ (Source or Model) መቀዳታቸውንና ስህተታቸውም ከተቀዱበት የተወረሰ (inherited) መኾኑን ይጠቁማሉ፡፡

### የብራና ቅጅዎችን ማቧደን (Grouping the Manuscript Copies)

ከላይ ቀደም ሲል እንደተገለጠው ቅጅዎች ያሏቸውን መጻሕፍት የትውልድ ሐረግ ለማሳየት ሁለትና ከዚያ በላይ የኾኑ ቅጅዎች (Copies) የተጋሩትን ዐቢይ ስህተት (Conjunctive error) በመጠቀም በቡድን በቡድን ወይም በየቤተሰቦቻቸው ማስቀመጥ የመጀመሪያው ቅድመ ኹኔታ ነው፡፡ ስለኾነም የዚኽ ጥናት ትኩረት የኾነው የመጽሐፈ እስክንድር ቅጅዎች (**ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ እና መ**) **ያላቸውን** ዝምድና ለማወቅ የአራቱን ቅጅዎች ውስጣዊ የጋራ ዐቢይ የገጸ ንባብ ስህተቶቻቸውን (Conjunctive error) በመለየት ዝምድናቸውን ከዚኽ በታች እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## የሦስቱ ቅጅዎች (ሀ፣ ለ እና ሐ) የጋራ የንባብ ስሕተት (Conjunctive error)

“ሀ”፣ “ለ”፣ እና “ሐ” ከቅጅ “መ” በተቃራኒ ከአንድ ቅጅ ለመቀዳታቸው ጠቋሚ ገጸ ንባብ ተጋርተዋል፡፡

1. ወእፈቅድ፡ ከመ፡ አእምር፡ ቃላቲሁ፡ እስመ፡ ይደልዎ፡ ከመ፡ አሀቦ፡ [ሥርጋዌ] ወእትዌከፎ።

*("ቃሉን አውቅ ዘንድ እወዳለሁ፤ ምክንያቱም [ሽልማት] እሰጠው ዘንድ እና በክብር እቀበለው ዘንድ ይገባዋልና፡፡")*

"ቃላቲሁ" የሚለው ቃል የዐረፍተ ነገሩን መልእክት ያዛባል ምክንያቱም ይኽ ዐረፍተ ነገር የተነገረበት ዐውድ ጦርነትን የሚመለከት ነው፡፡ በእስክንድርና በዳርዮስ መካከል በነበረው የጦር ፍልሚያ ዳርዮስ ተሸንፎ በመሸሽ ላይ እያለ በአንድ ወታደር በተገደለ ጊዜ ከእስክንድር ወታደሮች መካከል ዳርዮስን ማን እንደገደለው ስላልታወቀ እስክንድር ጠላቴን የገደለልኝ ማን ነው ብሎ ጠይቆ እንደነበር የእስክንድር ታሪክ ያስረዳል፡፡ ከዚኽ አንጻር ትክክለኛው ንባብ "ቃላታሁ" ('ቃሉን') የሚለው ሳይኾን በቅጅ "መ" ተመዝግቦ የሚገኘው "ቀታሊሁ" ('ገዳዩን') የሚለው ነው፡፡

**2.** ወይመልዕዎ፡ ወይነ፡ [ለልህኵት] ጊዜ፡ ይሠውዑ፡ ለአማልክት፡ ወጊዜ፡ ይገብሩ፡ ከዋክብተ።

('ለአማልክት *መሥዋዕት* በሚያቀርቡበትና ከዋክብት በሚያደርጉበት[15] ጊዜ [ሸክላ ውን] ወይን ይሞሉታል፡፡')

በዚኽ ዐውድ 'ከዋክብተ' የሚለው ቃል በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ ትርጉም አይሰጥም፤ ነገር ግን ትክክለኛው ንባብ በቅጅ "መ" ከብካባተ (ሰርግ) ሲል ይገኛል፡፡ የተሟላ የዐረፍተ ነገሩን ዐውድ የጠበቀና፣ ስሜት ሰጪ ንባቡም፤ "ለአማልክት *መሥዋዕት* በሚያቀርቡበትና ሰርግ በሚያደርጉበት ጊዜ [ሸክላውን] ወይን ይሞሉታል" የሚለው ነው፡፡

## ቅጅ "ሀ" እና "ለ" ከቅጅ "ሐ" እና "መ" በተቃራኒ የተጋሯቸው ስህተቶች

**1**. ወካዕበ፡ እዶ፡ እስክንድር፡ ውስተ፡ አፉሁ። ወይቤ፡ ተወሰከት፡ ሕይወትየ፡ ላዕለ፡ እዴከ።

*(ዳግመኛም እስክንድር እጁን ወደ አፉ፡፡ "ሕይወቴም በእጅህ ላይ ወደቀች" አለ፡፡)*

በዚኽ ምንባብ ዉስጥ በ "ሀ" እና በ "ለ" ቅጅዎች ዐረፍተ ነገሩ ያለማሰሪያ አንቀጽ ቀርቧል፡፡ ይኹን እንጂ በ "ሐ" እና "መ" ቅጅዎች አንበረ የሚል ማሰሪያ አንቀጽ እንደሚከተለው ተመዝግቦ ይገኛል፡፡፡

ወካዕበ፡ አንበረ እዶ፡ እስክንድር፡ ውስተ፡ አፉሁ። ወይቤ፡ ተወሰከት፡ ሕይወትየ፡ ላዕለ፡ እዴከ።

*(ዳግመኛም እስክንድር እጁን አፉ ላይ አደረገ (ጫነ)፡፡ "ሕይወቴም በእጅህ ላይ ወደቀች" አለ፡፡)*

ከዚኽ መረዳት የሚቻለው ቅጅ ሀ፣ ለ እና ሐ ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ወይም የዘር ሐረጋቸው አንድ ሲኾን "መ" ደግሞ ከእነዚኽ የተለየ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ቅጅ "ሐ" እና "መ" ከቅጅ "ሀ" እና "ለ" በተለየ መልኩ ከሌላ ቤተሰብ የተገኙ ናቸው፡፡ በመኾኑም "ሀ" እና "ለ" የቅጅ

**[15]ከዋክብት በሚቆጥሩበት ጊዜ ተብሎ ሊፈታም ይችላል ነገር ግን ዐውዱ ከኮከብ ቆጠራ የተለየ ስለኾነ ይኽን ትርጉም የተሻለ ኾኖ አላገኘኹትም፡፡**


ቅጅ ቅጅዎች ሲኾኑ ከዋናው ምንጭ በጣም የራቁ ናቸው፡፡ ይኸም ሐሳብም ከዚኽ በታች ባለው ሒሳባዊ ቀመር እንደሚከተለው ተገልጧል፡፡

**1.** $\beta$[16] = ሀ + ለ

**2.** $\alpha$ = $\beta$ + ሐ

**3.** $\Omega$[17] = $\alpha$ + መ

ሒሳባዊ ቀመሩን መሠረት በማድረግ የቅጅዎችን የትውልድ ሐረግ (Stemma codicum) ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡




## ማጠቃለያ

ጥናቱ የመጽሐፈ እስክንድርን የተለያዩ ቅጅዎች የዘር ሐረግ ወይም የቤተሰብ ዛፍና በቴክስት ትንተና ጊዜ ያለውን አንድምታ ያመላክታል፡፡ አራቱም ቅጅዎች ከአንድ ምንጭ የተቀዱ ቢኾኑም ሀ እና ለ የቅጅቅጅ ቅጅዎች ናቸው፡፡ ከዚኽ መረዳት የሚቻለው ከምንጫቸው በጣም የራቁ (the most corrupted texts) እና ለትንተና የማይመከሩ መኾናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩል ከኹለቱ ቅጅዎች መካከል “መ” እና “ሐ” በቅደም ተከተል ለአስገኛቸው ወይም ለተቀዱበት ምንጭ የቀረቡ ቅጅዎች ናቸው፡፡ ስለኾነም በንጽጽር የተሻለ ገጸ ንባብ ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በአጠቃላይ ቅጅዎች ያሏቸውን የእጅ ጽሑፎች (Manuscripts) እንዳገኙ ከመተርጎምና ለትንተና ከመጠቀም ይልቅ በቅድሚያ ቅጅዎችን መፈተሽና የቅጅ የሂደት ደረጃቸውንም (Copying stages) መለየት ጠቀሜታው እንዳለው መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

---

16 በዚኽ ሒሳባዊ ቀመር የቤተሰብ ዛፍ (Family tree or Stemma Codicum) ለማሳየት የተጠቀምኋቸው የግሪክ ፊደላት (Greek letters) α (አልፋ) እና β (ቤታ) የቅጅዎቻቸውን አስገኚ (Immediate ancestor) ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን አስገኛቸውም የጠፋ በመኾኑ ሐሳባዊ (hypothetical) ነው፡፡

17 ይኽ የግሪክ ፊደል Ω (ኦሜጋ) የሚጠቁመው ለአራቱም ቅጅዎች የመጀመሪያ ምንጭ ወይም አስገኝ መኾኑና ሞዴላቸውን በመጥፋቱ በቅጅ ቅጅዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፉንም መረዳት ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

አድማሱ ጀንበሬ፡፡ (1960)፡፡ የዲማ ቅ/ጊዮርጊስ የመጻሕፍት ቁጥር (ያልታተመ)፡፡ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (1948)፡፡ መጽሐፈ ሰዋስዉ ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ (1965)፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ (ናፓታ-መርዌ)፡፡ ሁለተኛ ዕትም፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ብርሃንና ሠላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

Daniel Ayana. (1989). A catalogue of Land tenure related Microfilm from Gojam Churches and Monasteries recorded between January and July 1989, No. 8.

Delamarter Steve, et. al. (2005). The Ethiopic Manuscript Imaging Project (EMIP) since 2005- 2010). George Fox University, Portland, Oregon, USA.

Lusini, Gianfransceco. (2003). "Alexander the Great". In S. Uhlig, Encyclopedia Aethiopica. Wiesbaden: Harrassowitz Vrlage

Maas Paul. (1958). Textual Criticism. Oxford: Clarendon Press.

Ministry of Education and Fine Arts, Department of Fine Arts and Culture (Addis Ababa). (1970). The Catalogue of manuscripts microfilmed by the UNESCO mobile microfilm unit in Addis Ababa and Goǧǧam Province. Addis Ababa.

Robins William. (2007). Editing and Evolution. Literature Compass. 4. (1). 89-120. Blackwell Publishing: University of Toronto.

Sidarus Adel Y. (2016). The Ethiopian Translations of Medieval Coptic Arabic Historiography: New Insights and Future Tasks. Journal of the Canadian Society for Coptic Studies. 8. PP. 33-41.

Tibebu Anteneh. (2020). The Ethiopic Version of the Alexander Romance by Pseudo Callisthenes: Critical edition with Annotated Translation. Unpublished PhD Dissertation. AAU.

Witzel Michael. (2014). Textual Criticism in Indology and in European Philology during the 19th and 20th centuries. Electronic Journal of Vedic Studies. 21(3),9-90.

Wolohogian Albert Mugrdich. (1969). The Romance of Alexander the Great by the Pseudo Callisthenes. New York and London: Columbia University Press.

Wright William. (1877). Catalogue of the Ethiopian Manuscripts in the British Museum acquired since the year 1847. London: The British Museum